# በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ

# ዋና የስራ ሂደት

## *(Revised TO-BE)*

**የአብክመ.ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከ/መቆ ማስ/ጽ/ቤት**

**(በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚያገለግል)**

መስከረም 2003 ዓ.ም.

<u>ባህር ዳር</u>

# 1. መግቢያ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የጤና ችግር ብቻ ሳይሆን ዘርፈ ብዙ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የፖለቲካዊ፣ የስነልቦናዊና በአጠቃላይም የልማት ችግር በመሆኑ፤ የሚያስፈልገውም ምላሽ እንዲሁ ዘርፈ ብዙና የሁሉንም ህብረተሰብ ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የክልሉ መንግስትም ዘርፈ ብዙ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችለው የክልሉን የኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤትና በስሩ ያሉ አደረጃጀቶችን ስልጣንና ተግባር የሚወስን አዋጅ በዝክረ ህግ አዋጅ ቁጥር 73/94 እና 89/1995 አውጥቷል፡፡ ይህንኑ አዋጅ መሰረት በማድረግ ለወረርሽኙ ዘርፈ ብዙ ምላሽ እየተሰጠ ያለ ቢሆንም የጥረቱ አድማስና ስፋት ከወረርሽኙ መስፋፋትና ፍጥነት ጋር ሲመዛዘን አሁን ካለው ጥረት በተፋጠነ ሁኔታ የዘርፈ ብዙውን የመከላከልና ቁጥጥር ስራ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ክልላችን በአገሪቱ ካሉ ሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ግንባር ቀደም ተጎጂ በመሆኑ እየተሰጠ ካለው ምላሽ የበለጠ ጥረት ካልተደረገ በቀር በሌሎች ልማቶቻችን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖውን የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ስለዚህ በአሰራር ሂደት ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ከተመረጡት ዋናዋና የስራ ሂደቶች ውስጥ አንዱ በጋራ ማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ የስራ ሂደት ነው፡፡

ይህ የስራ ሂደት በኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ስራ ውስጥ ሁሉንም አጋር አካላት በባለቤትነት ማሳተፍ ያስችላል፡፡ ዕቅዱ በማህበረሰብ ደረጃ ያሉ ሁሉንም አደረጃጀቶች መሰረት ያደርጋል፡፡ በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ባደረገው ዕቅድ ላይ የሚኖራቸውን የደጋፊነት ስራ ያካትታል፡፡ በጋራ ለተዘጋጀው ዕቅድ ማስፈፀሚያ የሚሆን የሃብት ክፍተትን በመለዮት ሀብት በማፈላለግ ፍትሀዊ ድልድል እንዲኖር ያደርጋል፡፡ የእቅድ አፈፃፀሙ በጋራ የክትትልና ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ በየደረጃው ያሉ የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችም በዚህ የስራ ሂደት የተዘረዘሩ ተግባራት እንዲወጡ የሚያስችል ሂደት ይኖራቸዋል፡፡ የዚህ የስራ ሂደት ዝርዝርም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- **የጥናቱ ዓላማ**

ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሁሉንም አካላት በጋራ በማሳቀድ፣ ዕቅድ ለማስፈፀም የሚያስችል

ሀብት በማሰባሰብ እና ክትትልና ግምገማ በማድረግ የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ አደረጃጀት መፍጠር ነው፡፡

## የጥናቱ አድማስ

- ጥናቱ ከማህበረሰቡ ጀምሮ እስከ ክልል ያሉትን አካላት በጋራ የማሳቀድ፣ የዕቅድ ማስፈፀሚያ ሀብት ማሰባሰብ እና ክትትልና ግምገማ የማድረግ ተግባራት የተሳሰሩ በመሆናቸው ሳይነጣጠሉ በሁሉም ደረጃ ያላቸውን ፍሰት የሚያሳይ ነው፡፡
- በማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ከተለዩት ዋናና ደጋፊ የሥራ ሂደቶች መካከል ይህ የስራ ሂደት የአሰራር ፍሰቱን ጠብቆ በተለያዩ ክፍሎች ተበታትነው የነበሩትን ስራዎች በአንድ በማሰባሰብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## የጥናቱ ዘዴ

- ከደንበኞች መካከል በናሙና የተመረጡ መ/ቤቶች መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ
- የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ሰራተኞችን ማነጋገር
- የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦችን መዳሰስ
- ለመሰረታዊ የስራ ለውጥ ሂደት ጥናት አጋዥ የሆኑ ዋቢ መጻህፍትን መቃኘትና የአሰራር መርሆዎችን መውሰድ
- በእቅድ ዝግጅት፣ ሀብት በማሰባሰብ እና በክትትል ግምገማ ዙሪያ የነበሩ አሰራሮችና ሰነዶችን መቃኘት
- ለመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ  ጥናት ከተመደቡ አማካሪዎች /ቄሳሮች/ ጋር በመወያየት ጥናቱ የተሰራ ሲሆን፤
- በሂደት በጥናቱ የሙከራ ትግበራ ወቅት ያጋጠሙና የተመዘገቡ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት የጥናቱ ክለሳ ተካሄዷል፡፡

## <u>ነባሩ በጋራ ማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የሥራ ሂደት አገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶች</u>

| ተ | የአገልግሎቱ አይነት | አሁን ያለበት ደረጃ | መሆን ያለበት |
|---|---|---|---|

| | | በመጠን | በጥራት | በጊዜ (በቀን) | በወጪ | በመጠን | በጥራት | በጊዜ (በቀን) | በወጪ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የዕቅድ ዝግጅትና ጥንቅር | 4920 (60%) | 70% | 69 | 2,158,200 | 8145 (100% ) | 100% | 40 | 1,079,00 |
| 2 | ፈንድ ማሰባሰብ | 10 | 50% | 11 | 2322 | 15 | 95% | 99 | 226025 |
| 3 | የበጀት ድልድል | 633 | 60% | 1387 | 290000 | 500 | 100% | 679 | 193013 |
| 4 | የዕቅድ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ | 1246+3442 =4687 | 37% | 623 | 1,439,130 | 32,580 | 100% | 19404 | 4,887,00 |
| 5 | የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ | 183 | 51% | 3X183 = 549 | 2152000 | 302 | 100% | 3X302 = 906 | 3,551,38 |
| 6 | በየደረጃው የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማጠናቀርና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ | 4 | 51% | 39 | 13400 | 4 | 100% | 10 | 3,350 |
| 7 | የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና ማካሄድና ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋት | 14 | 30% | 29 | 184000 | 69 | 82% | 212 | 387500 |

- **የስራ ሂደቱ ችግሮች፣ ህጎችና ታሳቢዎች (Problems, Rules & Assumptions)**

| ተ.ቁ (No) | ችግር (Problem) | የችግሩ ምንጭ (Rules) | ታሳቢዎች (Assumptions) |
|---|---|---|---|
| • | የእቅድ ዝግጅቱ የሕብረተሰቡን ተሳትፎና ፍላጎት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ለኤችአይቪ/ ኤድስ የተሰጠው ምላሽ ውጤታማነት ቀንሷል | በኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ ም/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 73/94 አንቀጽ 15 ን/ቁ. 9 መሰረት ዕቅድ ማዘጋጀት የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር በመሆኑ ይህን ተከትሎ በልማዳዊ አሰራር የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ሌሎች አካላትን በበቂ ሳያሳትፍ እያቀደ መሆኑ | የዕቅድ ዝግጅቱ በአስተባባሪው መ/( ቢዘጋጅ ከጊዜ፣ከሙያ፣ ከወጪና ከረጂዎች ፍላጎት አንጻር ውጤታማ ይሆናል የሚል እሳቤ በመኖሩ |
| • | ወረርሺኙ የሚጠይቀውን ያህል መጠነ ሰፊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል እቅድ ባለመዘጋጀቱ ፈጻሚ አካላት ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም አላስቻላቸውም | የረጂ ድርጅቶችን ሀብትና መመሪያ እንደብቸኛ የእቅድ ምንጭ አድርጎ የመውሰድ ልማዳዊ አሰራር መኖሩ | መጠነ-ሰፊ ምላሽ መስጠት የሚያስች በቂ የሆነ አቅም በታችኛው እርከን አይኖርም ብሎ ማሰብ |

የአፈጻጸም ክፍተትን፣ ችግሮች/ደንቦች/ታሳቢዎችንና የደንበኞችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በጥናት ቡድኑ አባላት የሚከተሉት አዳዲስ ሀሳቦች ፈልቀዋል፤

- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ የተጠናከረ የሚሆነውና ዘላቂነቱንም ለማረጋገጥ የሚቻለው የዕቅድ ዝግጅቱ ፈፃሚ አካላት በሚያቅዱት ዋናው ዕቅዳቸው ውስጥ አካተው ሲያቅዱት እንጂ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/ቁጥጥር ዕቅድ በሚል ለብቻው በማቀድ አይደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የክልሉን የልማት ዕቅድ የማሳቀድ ስልጣንና ኃላፊነት ስላለውና ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን የመከላከሉና መቆጣጠሩ ተግባርም አንዱ የልማት አጀንዳ በመሆኑ የመንግስት ሴክተሮች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዋናውን የልማት ዕቅዳቸውን አዘጋጅተው ለገ/ኢ/ል/ቢሮ ሲያቀርቡ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/ቁጥጥር አንፃር ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባራትም አካተው ሊያቅዱ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት፣
  - እንደማናቸውም የመንግስት የልማት ዕቅድ ሁሉ ወረዳዎች ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመከ/መቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራትን ከሌሎች የልማት ተግባራት ጋር አካተው በማቀድ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እንዲላክ ያደርጋሉ፣
  - በየወረዳዎች ያልተካተቱና ዘናዊም ሆነ ክልላዊ ይዘት ያላቸው ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመከ/መቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራት ደግሞ ከየሚመለከታቸው ሴክተሮችና በየደረጃው ካሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ከዋና የልማት እቅዳቸው ጋር ተካቶ እየተዘጋጀ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እንዲላክ ያደርጋሉ፣
  - የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮም እንደማንኛውም የልማት ዕቅድ ሁሉ ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመከ/መቆጣጠር እንዲያስችሉ የታቀዱ ተግባራትን ዕቅድ በማጠናቀር የተጠቃለለ ክልላዊ እቅድ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
- እያንዳንዱ ፈፃሚ፣ ሴክተር መ/ቤት በመደበኛነት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ጉዳይን የሚያስተባብር ሰው በመመደብ የፈፃሚውን ዕቅድ ያዘጋጃል ፣ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች በመንግስት ሴክተሮች ፎረም፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት በየዘርፋቸው በፎረሞች ተደራጅተው የየአባላቶቻቸውን ዕቅድ በማጠቃለል ለማስ/ጽ/ቤቱ ያቀርባሉ፡፡ እያንዳንዱ የሚቋቋምና የሚጠናከር ፎረም የራሱ የሆነ ተቋማዊ መዋቅር እንዲኖረው የሚደረግ ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙም፣
  - በቀበሌ ደረጃ የሚኖረው ፎረም/ፎረሞች/ በየዘርፋቸው ያዘጋጁትን ዕቅድ በማቅረብና በጋራ በማጠቃለል በቀበሌ ደረጃ በሚኖረው የኤችአይቪ/ ኤድስ አስተባባሪ (Focal Person) አማካኝነት ለወረዳ የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስ/ጽቤት ያቀርባሉ፣

- የየቀበሌዎች ዕቅድ በወረዳ የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስ/ ጽቤት ይጠቃለላል፤ አስተባባሪውም በወረዳ ደረጃ ለሚቋቋመው ፎረም ፀሀፊ እንደመሆኑ መጠን ከየቀበሌዎች የሚመጣውን እቅድ ታሳቢ አድርገው ወረዳዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ በቀበሌ ከተጠቃለለው ዕቅድ ጋር የወረዳ ዕቅድ ሆኖ ለዞን ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት ያቀርባል፣
- የዞን የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤትም ከየወረዳዎች የቀረበለትን ዕቅድ በማጠቃለል በዞን ደረጃ ፈጻሚዎች ካሉ ጨምሮ ለክልል ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ያቀርባል
- የክልል የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤትም ከየዞን የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት የመጣውን ለፎረሞች በማሳወቅና በክልል ደረጃ ከተቋቋሙ ፎረሞች ተዘጋጅቶ የቀረበውን ዕቅድ በማጠቃለል አንድ ክልላዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለክልሉ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/ መቆ/ ምክርቤትና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣

- ኤች.አይ.ቪ ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠሩ ተግባር ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎትና በሙሉ ተሳትፏቸው ላይ ተመስርቶ በቀበሌ ደረጃ ሲታቀድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት
  - በቀበሌ ደረጃ በሚዋቀር የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከ/መቆ ግብረ-ኃይል የቀበሌ እቅድ ተዘጋጅቶና ተጠቃልሎ ለወረዳ ይቀርባል፣
  - በወረዳ ደረጃ የየቀበሌዎች እቅድና በወረዳ ደረጃ ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት በወረዳ ፈጻሚዎች ታቅደው የተጠቃለለ ዕቅድ ለዞን ይቀርባል፣
  - ዞን ጽ/ቤት ከየወረዳ የመጣውን ዕቅድ በማጠቃለል ለክልል ያቀርባል፣
  - ክልል ጽ/ቤት ከየዞኖች የመጣውንና በክልል ደረጃ የታቀዱ ተግባራትን በማጠቃለል ክልላዊ ዕቅድ ማዘጋጀት
  - በክልል ደረጃ ከአጋሮች ጋር የዕቅድ አውደ ጥናት ማካሄድ፡፡
  - ለክልል ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፣

- ኤች.አይ.ቪ ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠሩ ተግባር ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የፈንድ ማሰባሰብና ሀብት ድልድል
  - እያንዳንዱ የስራ ሂደት የራሱን ተግባራት ለማስፈፀም የሚያስችል ሀብት ፕሮጅክት እየቀረፀ ፈንድ

ቢያፈላልግ ውጤታማ ስራ ለመስራት ይቻላል፣

- ለፈፃሚ አካላት የሚደረገው የፈንድ ድልድል/ስርጭት በኮታ ላይ የተመሰረተ ከሚሆን በዳሰሳ ጥናት ላይ ተመስርቶ ውጤት ሊያመጡ በሚችሉ ተግባራት ላይ ቢያተኩር፣
- በክልላችን ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመከ/መቆ ስራ ላይ እየዋለ ያለውን ሀብት በትክክል ለማወቅና ለመቆጣጠርም ያስችል ዘንድ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰባሰበው ሀብት ወደ ክልል ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ማስ/ጽ/ቤት ገቢ እየተደረገ ድግግሞሽን በሚያስወግድ መልኩ እንዲሰራጭ ቢደረግ፣
- በቂ ፈንድ ለማሰባሰብ ያስችል ዘንድ በበጀት መልኩ ከሚላክልን ገንዘብና ፕሮጀክት በመቅረጽ ከሚገኘው ፈንድ በተጨማሪ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞችን (ምሳሌ ሎተሪ ባዛር ወዘተ...) በማዘጋጀት ፈንድ ቢሰባሰብ፣
- በበጀት እና በዕርዳታ ላይ ተመስርቶ ሁል ጊዜ በቂ ፈንድ ማሰባሰብ ስለማይቻል የክልሉ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ማስ/ጽ/ቤት ዘላቂነት ባላቸው የገቢ ማስገኛ ተግባራት (እርሻ ልማት፣ ህንፃ ሰርቶ ማከራየት ወዘተ...) ላይ ቢሰማራ፣
- የተመላላሽ/ተዘዋዋሪ ፈንድ (revolving fund) ስርዓት ቢዘረጋና ተግባራዊ ቢደረግ እየተዘዋወረ ላልደረሳቸው ስለሚከፋፈል የፈንድ እጥረትን ከመቀነሱም በላይ የተረጂነት ስሜትን እንዳይኖርና፣ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል፣
- ከክልሉ መንግስት ዓመታዊ የስራ ማስኬጃ በጀት ላይ 2% እንዲመደብ ለማድረግ የሚያስችል አስገዳጅነት ያለው የህግ ማዕቀፍ ቢኖር፣
- ከሁሉም ሴክተሮች የሚሰባሰበው ኤድስ ፈንድ ወደ ክልሉ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ገቢ እየሆነ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት እንዲውል ቢደረግ፣
- ግልጽና ፍትሃዊ የሆነ የፈንድ ድልድል ለማድረግ ያስችል ዘንድ ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች እንደተሰባሰበ ፈፃሚ አካላት የበጀት ድልድሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ ቢደረግላቸው፣
- ፕሮጀክት በማዘጋጀት፣ 2% በጀትን፣ ኤድስ ፈንድን እንዲሁም ሌሎች የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በቂ ሀብት ለማሰባሰብ የሚያስችል አደረጃጀት ቢፈጠር፣
- ከተለያዩ አካላት የተገኘውን ገንዘብ ለተጠቃሚው የሀ/ሰብ ክፍል በወቅቱ ለማድረስ ያስችል ዘንድ የፕሮጀክት አፕሬዛል ሥራ በሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ ባለሙያዎች እየተገመገመ ገንዘብ እንዲለቀቅ ቢደረግ፤ ሆኖም ግን የለጋሽ ድርጅቶች ፍላጎት ፕሮጀክቶች በሪቪው ቦርድ እየታዩ ገንዘብ እንዲለቀቅ የግድ የሚል ከሆነ በዚሁ መሰረት ፕሮጀክቶች በሪቪው ቦርድ በገመገሙና ተቀባይነት ላገኙት ገንዘብ ቢለቀቅ፣

- ፕሮጀክት ቀርጾ ፈንድ የማፈላለጉ ተግባር ሀገር ውስጥ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ከሀገር ውጪም የሚሰባሰብበት ሁኔታ ቢኖር፣
- ተጨማሪ ፈንድ ለማሰባሰብ ያስችል ዘንድ ገንዘብ የሚለቀቅላቸው ፈፃሚ አካላት ቢያንስ የተለቀቀላቸውን ገንዘብ 10% ከራሳቸው ድርሻ ሊያዋጡ ይገባል፣

- የክትትል ስራ ያልተማከለ ሆኖ እንዲሰራ ነገር ግን በየደረጃው ላሉ ፈፃሚ አካላት ማለትም በክልል፣ በዞን፣በወረዳና በቀበሌ የሚደረገው ድጋፋዊ ክትትል በዕቅድ የሚመራና በቴክኖሎጂ የሚታገዝ መሆን ይኖርበታል፡፡ አፈፃፀሙ በዝርዝር ሲታይም፤
  - በቀበሌ ደረጃ የተዋቀረው ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ግብረ ሀይል የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ያደርጋል
  - የወረዳ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበርያ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ለወረዳ ፈጻሚዎችና ለየቀበሌዎች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣
  - የዞን ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ለዞን ፈጻሚዎችና ለወረዳዎች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣
  - የክልል ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበርያ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ለክልል ፈጻሚዎች ለዞኖችና ከዞኖች ጋር በመሆን በናሙና ለተመረጡ ወረዳዎች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣
  - ዘርፈ-ብዙውን ምላሽ ለማጠናከር ዋናዋና የክትትል ስራዎች ወሳኝ አካላትን ቢያካትቱ
  - እያንዳንዱ የክትትል ዓይነት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የክትትል ማዕቀፍ ቢኖሩት፣
  - ጊዜና ወጪን ከመቆጠብ አንጻር ክትትል በየደረጃው ባሉ ለክትትል በተዋቀሩ ቡድኖች ይከናወናል፤ በተለያዩ እርከኖች ያሉ አካላት በሪፖርትና በዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ይገናኛሉ፡፡ ከላይ ባለው የአደረጃጀት አካል በታችኛው የአደረጃጀት መዋቅር ላሉ አካላት በግንባር በመስክ ይደረግ የነበረው ድጋፋዊ ክትትል ይቀራል፡፡

- የሪፖርት አሰባሰብ ስርዓት የሴክተር መ/ቤቶች ከልማት ዕቅድ ሪፖርት ጋር አካትተው ለገ/ኢ/ል/ቢሮ፣ እንዲሁም የመያድ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲቀርብ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ዋናውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሪፖርት እንዲያጠናቅር፣ ሪፖርቶች በኮፒ ለኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ያደርሱታል፡፡
  - ሪፖርቶች የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀምን አካተው የሁሉንም ረጂ ድርጅቶች ፍላጎት የሚያካትቱ ቢሆኑ

- የሪፖርትን ወቅታዊነት ለማስጠበቅ በዞን ደረጃ ያለውን የሪፖርት በኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤት ማፅደቅ ሂደትን ማስቀረት ቢቻል፣
- የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሥራ ዕቅድና ሪፖርት በገ/ኢ/ል/ቢሮ ሆኖ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ የማስተባበሪያ ጽ/ቤት ድርሻ ቅፃቅፆችን፣ የተግባር ዝርዝሮችንና አመላካቾችን ማዘጋጀት የሪፖርትን ወቅታዊነትና ጥራት ለማስጠበቅ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በሪፖርት ስርዓት መጠቀም ቢሆን፣
- የሪፖርት ሰንሰለቱ፤
    - የቀበሌ ሪፖርት በየፈፃሚ አካላቱ ተዘጋጅቶና በቀበሌው አስተባባሪ ተጠቃልሎ በቀበሌ አስተዳድሩ ፀድቆ ለወረዳ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና ለቀበሌ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ምክር ቤት ይላካል
    - ወረዳ ከቀበሌ የመጡ ሪፖርቶችንና በወረዳ ደረጃ ለተፈፀሙ ተግባራት ከየፈፃሚዎቹ የተዘጋጁ ሪፖርቶችን በማጠቃለል ለዞን ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤትና ለወረዳ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ምክር ቤት ይልካል፣
    - ዞን ጽ/ቤት የየወረዳዎችን በማጠቃለል ለክልልኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይልካል
    - የክልሉ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበርያ ጽ/ቤት በክልል ደረጃ ለተፈፀሙ ተግባራት ከክልል ፈፃሚዎቹ የተዘጋጁ ሪፖርቶችንና ከየዞኑ የተሰባሰቡ ሪፖርቶችን በማጠቃለል ለክልሉ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ ምክር ቤትና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል/ ይልካል፣
    - ለየኔትወርኮች (የግንኙነት መረቦች) አስፈላጊ የሆኑ የሪፖርት ቅፃቅጽ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተዘጋጅተው ኔትወርኮቹ ሪፖርት ለኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እያቀረቡ አጠቃላይ ሪፖርት ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይጠናቀራል፣
- የፊዚካልና ለለጋሾች የሚቀርቡ ፋይናንስ ሪፖርቶች በአንድ የስራ ሂደት ስር ቢደራጁ፤
- ለጊዜ ቁጠባ ሪፖርቶች ሲላኩ ጠብቆ ከመቀበል በየደረጃው በመንቀሳቀስ መሰብሰብ ቢቻል፤
- ሪፖርት የዕቅዱን ፍሰትን ተከትሎ ከቀበሌ እስከ ክልል ባሉ ፈጻሚዎች ቢዘጋጅና በኤችአይቪ/ኤድስ የመከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች እየተጠቃለለ ቢሰራጭ፤
- ኤችአይቪ/ኤድስን የመከ/መቆ/ ስራዎች የሁሉንም አካላት ርብርብ የሚጠይቁ በመሆናቸው በምክር ቤቱ ሰብሳቢ የቅርብ እገዛ እንዲያገኙ በየደረጃው በአስተዳደር መዋቅር ስር ቢደራጁ፤
- የጤናው ሴክተር ለኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሥራ ከሚመደበው በጀት ከፍተኛ ድርሻ ስለሚወስድ ጤና ነክ ያልሆነውን የኤችአይቪ/ኤድስ ስራ ጨምሮ ጤና ጥበቃ ስር ቢደራጅ፤

- የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤቶች አደረጃጀት ጊዜ ወሳጅ በመሆኑ ቢቀርና ስራው እራሱን በቻለ አንድ አስተባባሪ መ/ቤት ቢመራ፤
- ጤና ነክ የሆነውን የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ስራ የጤና ጥበቃ ቢሮ ጤና ነክ ያልሆነውን የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ስራዎች የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ ወስዶ ሌሎቹን አካላት ቢያስተባብር፤
- የምስራቅ አማራን አምስት ዞኖች በቅርበት ለማስተባበር እንዲቻል የክልሉ አንድ ንዑስ ቅርንጫፍ ቢከፈት፤
- ጥናታዊ ግምገማን በተመለከተ
    - አዳዲስ የአሰራር ሥልቶች አዋጭነታቸው በጥናት ሳይረጋገጥ ወደ አፈጻጸም ባይገባ፣
    - እንደ ጉዳዩ አንገብጋቢነት በዝርዝር ጥናት ሳይሆን በመስክ ምልከታዎች በተገኙ መረጃዎች ላይም ተመርኩዞ አድቮኬሲ ማካሄድ ቢቻል፣
    - ጥሩ ተሞክሮዎች በሙሉ ቢዘገቡ፣
    - ነባሮቹ የኤች.አይ.ቪ. መከ/መቆ/ ተግባራት አዋጭነታቸው በጥናት ቢረጋገጥ፣
    - በጥናቶች ላይ የተጠቆሙ መፍትሄ ሀሳቦችና ግኝቶች በወቅቱ ወደ ተግባር የሚለወጡበት አካሄድ ቢኖር
    - ሁሉም የአድቮኬሲ ስራዎች በጥናት ላይ የተመሰረቱ ቢሆኑ፤

## *5.2 በተደራጀ መልክ የወጡ አዲስ ሀሳቦች*

ከላይ ከተራ ቁ. 1-12 በቀረቡት አዳዲስ ሀሳቦች ላይ የጥናት ቡድኑ ሰፊ ውይይት ካካሄደ በኋላ የስራ ሂደቱን በተመለከተ ዕቅድ፣ ሀብት ማሰባሰብና ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ከጫፍ እስከ ጫፍ ለማስኬድ በሚያስችል መልኩ በሰባት ዋናዋና አማራጮች ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡ እነዚህም፤

1ኛ. የመንግስት ሴክተሮች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዕቅድና ሪፖርት እንደማንኛውም የልማት ዕቅድ ሁሉ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አማካይነት ፣ የሌሎች ማህበራትና ተቋማት ደግሞ በየሚመለከታቸው የመንግስት ተቋም አማካይነት ተጠቃልሎ እንዲመጣና ክትትሉን በተመለከተ ግን የማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊነት እንዲሆን ቢደረግ፤

2ኛ. ሁሉም ፈጻሚና አጋር አካላት በትብብር መድረኮች እንዲደራጁና የፈጻሚዎች ዕቅድና ሪፖርት በነዚህ አካላት እየተጠቃለለ ለማስተባበሪያ ጽ/ቤት ቢቀርብና ጽ/ቤቱ የነዚህን የትብብር መድረኮች ዕቅድና ሪፖርት በማጠቃለል ክልላዊ መልክ እየሰጠው ክትትል ቢያደርግበት፤

3ኛ. ዕቅድ ሁሉንም የህብረተሰቡ አደረጃጀቶችና መዋቅሮች ባሳተፈ መልኩ ከቀበሌ ጀምሮ እየታቀደና እየተጠቃለለ

እስከ ክልል ቢመጣ፣ ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ በቂ ሀብትም በማሰባሰብና ፍትሀዊ ድልድል በማድረግ ቢቀርብ እና ክትትልም በየደረጃው በሚቋቋሙ የክትትል ቡድኖችና ባለሙያዎች ሪፖርትም በተመሳሳይ ከቀበሌ እስከ ክልል በፈጻሚዎች እየተዘጋጀና በኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት መዋቅሮች አማካይነት እየተጠቃለለ የሚቀርብ ሆኖ በጥናት ላይ ተመሰርቶ መስራትና ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋት በሚል ስራዎች ቢደራጁ

4ኛ. ኤችአይቪ/ኤድስን የመከ/መቆ/ ስራዎች የሁሉንም አካላት ርብርብ የሚጠይቁ በመሆናቸው በምክር ቤቱ ሰብሳቢ የቅርብ እገዛ እንዲያገኙ በየደረጃው በአስተዳደር መዋቅር ስር ቢደራጁ፤

5ኛ. የጤናው ሴክተር ከኤችአይቪ/ኤድስ በጀት ከፍተኛ ድርሻ ስለሚወስድ ጤና ነክ ያልሆነውን የኤችአይቪ/ኤድስ ስራ ጨምሮ ጤና ጥበቃ ስር ቢደራጅ፤

6ኛ. የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤቶች አደረጃጀት ጊዜ ወሳጅ በመሆኑ ቢቀርና ስራው እራሱን በቻለ አስተባባሪ አካል ቢመራ፤

7ኛ. ጤና ነክ የሆነውን የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ስራ የጤና ጥበቃ ቢሮ ጤና ነክ ያልሆነውን የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ስራዎች የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ ወስዶ ሌሎቹን አካላት ቢያስተባብር፤

ከዚህ በላይ ከተጠቃለሉት ሰባት አማራጮች መካከል የመጀመሪያዎቹ (በተራ ቁ.1፣2፣3 የተቀመጡት) ሦስት ሃሳቦች በአማራጭነት ለማወዳደር ተመርጠዋል፡፡

- **<u>በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የስራ ሂደት</u>**

ለውድድር የቀረቡ ሦስት ሃሳቦች የስራ ሂደት ፍሰት (High Level Map)

### *6.1. አማራጭ 1 የስራ ፍሰት (High Level Map)*

የዕቅድ መነሻ ማዕቀፍ ይዘጋጃል

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያቅዳሉ

በየደረጃው ዕቅድ ይጠቃለላል

የመንግስት ሴክተሮች ያቅዳሉ

በየደረጃው የዕቅድ አውደ ጥናት ይካሄዳል

የለም

ዕቅድ ይፀድቃል

አዎ

ድጋፋዊ ክትትል ይካሄዳል

የመያድ ሪፖርት ይዘጋጃል

ፈጻሚዎች ሪፖርት ያዘጋጃሉ

ሪፖርት ይጠቃለላል

## 6.2 ***አማራጭ 2 የስራ ፍሰት (High Level Map)***

የዕቅድ መነሻ ቴምፕሌት ይዘጋጃል

ፈጻሚዎች ያቅዳሉ

በየደረጃው በትብብር መድረኮች ዕቅድ ይጠቃለላል

በየደረጃው በጽ/ቤቱ ዕቅድ ይጠቃለላል

ዕቅድ ይፀድቃል

የለም

ድጋፍ ይደረጋል

አዎ

ወደ ጎንና ወደታች ድጋፋዊ ክትትል ይካሄዳል

ፈጻሚዎች ሪፖርት ያዘጋጃሉ

ሪፖርት ይጠቃለላል

## *6.3 <u>አማራጭ 3 የስራ ፍሰት (High Level Map)</u>*

የዕቅድ መነሻ ቴምፕሌት ይዘጋጃል

በየደረጃው ዕቅድ ይጠቃለላል

ፈጻሚዎች ያቅዳሉ

ዕቅድ ይፀድቃል

የለም

አዎ

የሀብት ምንጮች
የዕቅድ ማስፈፀሚያ ሀብት ማሰባሰብና ድልድል ማድረግ
ድጋፍ ይደረጋል

ወደ ጎንና ወደታች ድጋፋዊ ክትትል ይካሄዳል

ፈጻሚዎች ሪፖርት ያዘጋጃሉ

ሪፖርት ማጠቃለልና የፕሮግራም ውጤታማነትን መገምገም

የቀበሌ ዕቅድ  በወረዳ ደረጃ ማጠቃለል

የለም
ከቀበሌዎችና ከወረዳ ፈፃሚዎች የመጣው ዕቅድ በወረዳ ደረጃ ማጠቃለል
በወረዳ ደረጃ ያሉ ፈፃሚዎችን ያሳተፈ የዕቅድ ምክክር አውደ ጥናት ማካሄድ

የሃብት ምንጭ

ሀብት ማሰባሰብና ድልድል ማድረግ

ፈፃሚዎችን መደገፍ

አዎ

ዕቅዱ በዞን  ማስ/ጽ/ቤት ማጠቃለል

የሃብት ምንጭ

የለም

ሀብት ማሰባሰብና ድልድል ማድረግ

ዕቅዱ በዞኑ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤት ማስጸደቅ

ፈፃሚዎችን መደገፍ

አዎ

ፈፃሚዎችና አጋሮች ደጋፊ  ዕቅድ ማዘጋጀት

በተጠቃለለው ዕቅድ ላይ ከክልል ፈጻሚዎችና አጋሮች ጋር የዕቅድ አውደ ጥናት ይካሄዳል

በክልል ደረጃ የየዞኑ ዕቅድ ማጠቃለል

የሃብት ምንጭ

ሀብት ማሰባሰብና ድልድል ማድረግ

ዕቅዱ በክልሉ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤት ማስጸደቅ

አዎ

የለም

ፈፃሚዎችን መደገፍ

ዕቅድ ለሚመለከታቸው ማሰራጨት

የዞንና የክልል ፈፃሚዎችና አጋሮች ዕቅድ ማጠቃለል

ዕቅድ ለቦርድ ማቅረብ

1

በየደረጃው የጎንዮሽና ወደታች የጋራ ድጋፋዊ
ክትትል ማድረግ
የፈፃሚዎች
የትግበራ ሂደት
ግብረ መልስ መስጠት
የክትትል ቢጋር ማዘጋጀት

የክትትል ሪፖርት ማዘጋጀት

በዞን ጽ/ቤት የየወረዳዎች ሪፖርት ማጠቃለል
የቀበሌና የወረዳ ፈፃሚዎች ሪፖርት በወረዳ ማጠቃለል
በወረዳ ደረጃ የቀበሌ ሪፖርት ማጠቃለል
ሁሉን አቀፍ የሪፖርት ማዕቀፍ ማዘጋጀት

ፈጻሚዎች

በየስድስት ወሩ ሪፖርት በኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤት ማስጸደቅ

የዕቅድ አፈጻጸምና የፕሮግራም ውጤታማነት ግምገማ ማካሄድ

የክልል ፈፃሚዎችና የዞኖች ሪፖርት በክልል ደረጃ ማጠቃለል
ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት መላክ

የለም

አዎ
ሪፖርት ለሚመለከታቸው ማሰራጨት

ሪፖርት ፈላጊዎች

| | | |
|---|---|---|
| **4** | አራት  የዕቅድና ሪፖርት በም/ቤት የማስጸደቅ እርከኖች ነበሩ | በየደረ ዞንና በ |
| 5 | የሚሰባሰበው ፈንድ ከፌደራል ጽ/ቤትና ከክልሉ መንግስት በሚላከው በበጀት ላይ ብቻ ስለነበር በቂ ፈንድ ለማሰባሰብ አላስቻለም | ከፌደራ በፕሮጀ ፈንድ |
| 6 | ከተለያዩ የበጀት ምንጮች የተሰባሰበው ፈንድ ለመደልደል ለሚመለከታቸው ፈፃሚ አካለት ጥሪ ስለማይደረግ ግልፅነትና ፍትሀዊነት ይጎድል ነበር | የፈንድ የሆነ ግ |
| **7** | የድጋፋዊ ክትትል አገልግሎት የሚያገኙ አካላት ቁጥር ውሱንና ወቅቱም የማይታወቅ ነበር | በዕቅድ ስርዓት |
| **8** | ለመስክ ክትትል ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ ግብረመልስ መስጠት እንደግዴታ ስራ አይታይም ነበር | ለመስክ ማዕቀፉ |
| **9** | ክትትል የሚደረግበትን ደረጃና መጠን የተወሰነ አልነበረም | ክትትል ጠቀሜ ወረዳዎ ፈጻሚያ |
| **10** | ቋሚ የሆነ የጋራ ክትትል አልነበረም | በየደረ ውጤታ |
| **11** | ሪፖርት አሰባሰቡ ተደጋጋሚና እንደ ሪፖርት ተቀባዩ ፍላጎት የተለያየ ነበር | ሪፖርት በመሆኑ |
| **12** | ለለጋሾች የሚቀርብ የፊዚካል ሪፖርት በተለያየ ክፍል ይጠናቀሩ ነበር | ለለጋሾ ይጠቃለ |
| **13** | በክልሉ የኤችአይቪ ኤድስ መከ/መቆ/ ተግባራት የሚውለውን አካባቢያዊ ሀብት፣ የበጀት ክፍተት እንዲሁም በአጠቃላይ ስራ ላይ የዋለውን ሀብት ማወቅ አይቻልም ነበር፡፡ | በክልሉ ሀብት፣ ማወቅ |
| **14** | ታቅዶ የሚካሄድ ጥናትና የፕሮግራም ውጤታማነት ግምገማ አልነበረም | ጥናት፣ ይሆናሉ |

- <u>በአዲሱ የስራ ሂደት ጥናት መሰረት የሚቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የሚገባቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመርያዎች</u>

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3.1. | የሪፖርት ማሰባሰቢያ ቅጽ ማዘጋጀት/መከለስ | ወቅታዊ ሪፖርት የማቅረብ ፍላጎት | የተሟላ መረጃ ማሰባሰብ የሚያስችል የሪፖርት ቅጽ | ለደንበኞች ወቅታ ጥራት ያለው ሪፖ ማቅረብ |
| 3.2 | የቀበሌ ሪፖርት በወረዳ ደረጃ ማጠቃለል | የተጠቃለለ የቀበሌ ሪፖርት ፍላጎት | የተጠቃለለ የቀበሌ ሪፖርት | የሪፖርት ፈላጊ ደንበኞ ፍላጎት ማርካት |
| 3.3 | በወረዳ ደረጃ ሪፖርት ይጠቃለላል | በወረዳ ደረጃ ያለውን አፈፃፀም የማወቅ ፍላጎት | በወረዳ ደረጃ የተጠቃለለ ሪፖርት | የሪፖርት ፈላጊ ደንበኞ ፍላጎት ማርካት |
| 3.4 | ከየወረዳዎች የተሰባሰበ ሪፖርት በዞን ይጠቃለላል | በየዞኑ ያለውን አፈፃፀም የማወቅ ፍላጎት | በየዞኑ የተጠቃለለ ሪፖርት | የሪፖርት ፈላጊ ደንበኞ ፍላጎት ማርካት |
| 3.5 | ከየዞን ጽ/ቤቶችና በክልል ደረጃ ካሉ ፈጻሚአካላት የተሰባሰበ ሪፖርት በክልል ደረጃ ይጠቃለላል | በክልል ደረጃ ያለውን አፈፃፀም የማወቅ ፍላጎት | በክልል ደረጃ የተጠቃለለ ሪፖርት | የሪፖርት ፈላጊ ደንበኞ ፍላጎት ማርካት |
| 3.6 | ሪፖርት ለየሚመለከታቸው አካላትና ለረጂ ድርጅቶች ተደራጅቶ ይላካል | የረጂዎችናዘዘ አጋሮች ሪፖርት የማግኘት ፍላጎት | ሪፖርት ለሚጠብቁ ሁሉ ይደርሳል | የሪፖርት ፈላጊ ደንበኞ ፍላጎት ማርካት |
| **4** | **የዕቅድ አፈጻጸምና የፕሮግራም ውጤታማነት ግምገማ ማካሄድ** | | | |
| 4.1 | የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ስብሰባ | በጋራ የእቅድ አፈጻጸምን ደረጃ የመገምገም ፍላጎት | የጋራ ስምምነት የተደረሰበት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት | የተሻለ አገልግ አሰጣጥ ለመስ መነሳሳት |
| 4.2 | የፕሮግራም ውጤታማነት ግምገማ ማካሄድ | የፕሮግራም ውጤታማነት የማወቅ ፍላጎት | ውጤታማነቱ የተገመገመ ፕሮግራም | ውጤታማ አሰራር |
| 4.3 | ሪፖርት ለክልል ኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ ምክር ቤት ይቀርባል | ክልላዊ አፈጻጸምን የማወቅ ፍላጎት | በክልል ኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/ መቆ/ ም/ቤት የጸደቀ ሪፖርት | ለኤችአይቪ ኤ መከ/መቆ/የተጠናከረ ምላሽ መሰጠቱ |
| 4.4 | በም/ቤት የፀደቀ ሪፖርትና የፕሮግራም ውጤታማነት ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት | የአጋሮች ሪፖርትና የፕሮግራም ውጤታማነት የማግኘት ፍላጎት | የቀረበ ሪፖርት | የሪፖርት ፈላጊ ደንበኞ ፍላጎት ማርካት |

- **<u>በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የስራ ሂደት የአፈፃፀም ስታንዳርድና ፈፃሚዎች</u>**

| ተ.ቁ | የሂደቱ ዋናዋና ተግባራትና ዝርዝር ስራዎች | ስራዎቹ የሚሰሩበት ቦታ | ስራዎቹ የሚሰሩበት ወቅት | ስራዎቹ የሚወስዱት ቀናት |
|---|---|---|---|---|
| **1.** | **የዕቅድ ዝግጅት** | | | |
| 1.1 | **የዕቅድ ማዕቀፍ/ቴምፐሌት/ ማዘጋጀት** | ክልል ማስ/ጽ/ቤት | ሚያዝያ | |
| | • አስቀድሞ የተዘጋጁ የዕቅድ ሰነዶችን ማሰባሰብ | >> | >> | 2 |
| | • የሁሉንም ደንበኞች ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ድራፍት የዕቅድ ማዕቀፍ ማዘጋጀት | >> | >> | 5 |
| | • ዕቅድ ማዕቀፉ ድራፍት ላይ ከጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር መመካከር | >> | >> | 1/2 |
| | • የእቅድ ማዕቀፉን ማጠናቀቅ | >> | >> | 5 |
| | • የአስተቃቀድ ማብራሪያዎችን ማዘጋጀት | >> | >> | 3 |
| | • የእቅድ ማዕቀፉን ማሰራጨት | >> | >> | 1/2 |
| 1.2 | **የዕቅድ አዘገጃጀት ገለጻ (ወረዳዎች ለየቀበሌ ተጠሪዎች)** | **ወረዳ** | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • የዕቅድ ማዕቀፉንና ማብራርያዎቹን በተሳታፊዎቹ ቁጥር ማባዛትና ቅድመ ዝግጅት | ወረዳ ማስ/ጽ/ቤት | ሚያዝያ | 1 |
| | • ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ | >> | >> | 3 |
| | • ገለፃ መስጠት፣ የዕቅድ ማዕቀፉን ማሰራጨት | >> | >> | 1 |
| **1.3** | **ዕቅድ ዝግጅት በቀበሌ ደረጃ** | | | |
| | • ለቀበሌ ፈፃሚዎች ጥሪ ማስተላለፍ | በቀበሌ ፈጻሚዎች | ግንቦት | |
| | • የዕቅድ አዘገጃጀት ገለፃና የማዕቀፍ ስርጭት ማድረግ | | >> | |
| | • ፈፃሚዎች ዕቅድ ያዘጋጃሉ(በአማካይ 3 ቀን) | | >> | |
| | • ዕቅድን በቀበሌ ደረጃ ማጠቃለልና መላክ | | >> | |
| **1.4** | **ዕቅድ ዝግጅት በወረዳ ደረጃ** | | >> | |
| | • የቀበሌዎችን ዕቅድ ማጠናቀር | ወረዳ ማስ/ጽ/ቤት | >> | **2** |
| | • ለወረዳ ፈፃሚዎች ጥሪ ማስተላለፍ | >> | >> | **½** |
| | • ለወረዳ ፈጻሚዎች በተጠቃለለው የቀበሌ ዕቅድ ላይ ገለፃ ይካሄዳል | >> | >> | **½** |
| | • የወረዳ ፈፃሚዎች ዕቅዳቸውን ያዘጋጃሉ (በአማካይ 3 ቀን) | >> | >> | |
| | • ዕቅድን በወረዳ ደረጃ ማጠቃለል | >> | >> | **3** |
| | • ዕቅድን በወረዳ ደረጃ ማስፀደቅ | >> | | **1** |
| | • በወረዳ ደረጃ የተጠቃለለ እቅድ ለዞንና ለሚመለከታቸው አካላት ይተላለፋል | >> | >> | **¼** |
| **1.5** | **ሀብት ማሰባሰብና ድልድል በወረዳ ደረጃ** | | | |
| | • በወረዳ ደረጃ ሀብት ማሰባሰብ | ወረዳ ማስ/ጽ/ቤት | ዓመቱን ሙሉ | **8** |
| | • በወረዳ ደረጃ ሀብት መደልደል (በዕቅድ ወቅት ያልታዩ የአፕሬዛል ስራዎችን ይጨምራል) | >> | >> | **42** |
| **1.6** | **ዕቅድ ማጠቃለል በዞን ደረጃ** | | >> | |
| | • የወረዳዎችን ዕቅድ ማጠናቀር | በየዞኖች | ግንቦት | 3 |
| | • ለዞን ፈፃሚዎች ጥሪ ይተላፋል | >> | >> | ¼ |
| | • ለዞን ፈጻሚዎች በተጠቃለለው የወረዳ ዕቅድ ላይ ገለፃ ይካሄዳል | >> | >> | **½** |
| | • የዞን ፈፃሚዎች ዕቅዳቸውን ያዘጋጃሉ (በአማካይ 3 ቀን) | >> | >> | |
| | • ዕቅድን በዞን ደረጃ ማጠቃለል | >> | >> | **3** |
| | • ዕቅድን በዞን ደረጃ ማስፀደቅ | >> | | **1** |
| | • በዞን ደረጃ የተጠቃለለ እቅድ ለክልልና ለሚመለከታቸው አካላት ይተላለፋል | >> | >> | **¼** |
| **1.7** | **ሀብት ማሰባሰብና ድልድል በዞን ደረጃ** | | | |
| | • በዞን ደረጃ ሀብት ማሰባሰብ | በየዞኖች | ዓመቱን ሙሉ | **4** |
| | • በዞን ደረጃ ሀብት መደልደል (በዕቅድ ወቅት ያልታዩ የአፕሬዛል ስራዎችን ይጨምራል) | >> | >> | **42** |
| **1.8** | **በክልል ደረጃ ዕቅድ ማጠቃለልና ማስፀደቅ** | | | |
| | • ከየዞኖች የመጣውን ዕቅድ ማጠቃለል | ክልል | ሰኔ | 8 |
| | • ለክልል ፈፃሚዎች ጥሪ ይተላፋል | >> | >> | ¼ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • ከክልል ፈጻሚዎች ጋር የዕቅድ ዝግጅት ዓውደ ጥናት ይካሄዳል | >> | >> | 1 |
| | • የክልል ፈፃሚዎችና አጋሮች ደጋፊ ዕቅድ ዝግጅት (በአማካይ 3 ቀን) | >> | >> | |
| | • ክልላዊ ዕቅድ ይጠቃለላል | >> | >> | 3 |
| | • ዕቅዱ ለክልሉ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/ መቆ/ ምክር ቀርቦ የፀድቃል | >> | >> | 1 |
| | • በክልል ደረጃ የፀደቀ እቅድ ለፌዴራልና ለሚመለከታቸው አካላት ይተላለፋል | >> | >> | ¼ |
| **1.9** | **ሀብት ማሰባሰብ በክልል ደረጃ** | | | |
| | የፌደራል ጽ/ቤትና የክልሉ መንግስት የሚሸፍኑትን በጀት ያሳውቀሉ | ፌደራልና የክልሉ መንግስት | መጋቢት | ---- |
| | በፌደራል ጽ/ቤትና በክልሉ መንግስት በጀት ያልተሸፈኑ ተግባራትን መለየት | ክልል | መጋቢት | 1 |
| **1.9.1** | **በፕሮጀክት ቀረጻ የሚሰባሰብ ሀብት** | | | |
| | ፕሮጀክት ለመቅረጽ የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብ፣ መተንተንና ማጠናከርና | ክልል | ዓመቱን በሙሉ | 10 |
| | ፕሮጀክት መቅረፅ (በዓመት 8 ፕሮጀክቶች ቢቀረፁ) 8 ፕሮጀክት X ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት 5 ቀን | >> | >> | 40 |
| | የተቀረጸውን ፕሮጀክት ለድጋፍ ሰጭ አካላት መላክ | >> | >> | 1 |
| | ለለጋሽ ድርጅቶች የተላከው ፕሮጀክት በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ክትትል ማድረግ | >> | >> | 2 |
| | የተላው ፕሮጀክት ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ ለጋሽ ድርጅቶች ያሳውቃሉ | ለጋሾች | >> | ---- |
| | ለጋሽ ድርጅቶች አዘጋጅተው የሚልኩትን የውል ስምምነት መፈረም | ክልል | >> | 2 |
| **1.9.2** | **ከዩንዳፍ የሚገኝ በጀትን በተመለከተ** | | | |
| | የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከዩንዳፍ የመጣለትን ሀብት በማሳወቅ የሀብት መጠየቂያ እንዲቀርብ ያሳውቃል | ክልል | በየሩብ ዓመቱ | ---- |
| | የክልል ማስ/ጽ/ቤት የሀብት መጠየቂያ ቅጽ በመሙላት ለቢሮው ያሳውቃል | >> | በየሩብ ዓመቱ | 2 |
| | ቢሮው የቀረበለትን የገንዘብ መጠየቂያ ለለጋሽ ድርጅቶች ይልካል፣ ገንዘብ መግባቱንም ይከታተላል፣እንደገባም ለጽ/ቤታችን ያሳውቃል | >> | በየሩብ ዓመቱ | ------- |
| | ቢሮው ገንዘብ መግባቱን እንዳሳወቀን ለክልል ማስ/ጽ/ቤትና ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶች ገንዘብ ለማስተላፍ የሚያስችል ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ለቢሮው ይቀርባል | >> | በየሩብ ዓመቱ | 4 |
| **1.9.3** | **የመንግስት መደበኛ በጀትን በተመለከተ** | | | |
| | ቢሮው በሚያሳውቀው ጊዜያዊ የበጀት ጣሪያ መሰረት በየበጀት አርዕስቱ ድልድል ተደርጎ ይላከለታል | ክልል | ሚያዚያ | 1 |
| | ቢሮው ዓመታዊ የክልሉን በጀት በምክር ቤት በማፀደቅ ትክክለኛውን ዓመታዊ በጀት ያሳውቃል | >> | ሚያዚያ | ----- |
| | ቢሮው በምክር ቤት የፀደቀውን በጀት እንዳሳወቀን የማስተካከያ የበጀት ድልድል ይሰራል | >> | ሚያዚያ | ½ |
| 1.10 | ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች የሚሰባሰበው ሀብት ወደ ባንክ እንዲገባ ክትል ማድረግና የገባ መሆኑን ማረጋገጥ | >> | ዓመቱን በሙሉ | 4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **2.** | **የሃብት ድልድል ማድረግ** | | | |
| 2.1 | የበጀት ድልድል ለማድረግ ለዞን ማስ/ጽ/ቤቶችና ለክልል ፈጻሚ አካላት ጥሪ ይተላለፋል፣ | ክልል | ግንቦት | ½ |
| 2.2 | ለውይይት መነሻ የሚሆን የሀብት ድልድል ፕሮፖዛል ይዘጋጃል | >> | ግንቦት | 8 |
| 2.3 | በቀረበው መነሻ ሀሳብ መሰረት በተሳታፊዎች ውይይት ተካሂዶ ድልድሉ ይሰራል | >> | ግንቦት | 2½ |
| 2.4 | የተሰራውን የሀብት ድልድል ለሚመለከታቸው ማሳወቅ | >> | ግንቦት | ½ |
| 2.5 | በዕቅድ ዝግጅት ወቅት ያልታዩ የአፕሬዛል ስራዎች | >> | ዓመቱን በሙሉ | 80 |
| **3** | **ድጋፋዊ ክትትል** | | | |
| | • የክትትል ቢጋር ማዘጋጀት | ክልል፣ ዞንና ወረዳ | ሐምሌ | **2** |
| | • የመስክ ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ | | | |
| | • ክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት (120 ፈፃሚ x 4 ጊዜ x 1.5ቀን) | ክልል | በየሩብ ዓመቱ | 720 |
| | • ዞን ማስ/ጽ/ቤት (50 ፈፃሚ x 4ጊዜ x 1 ቀን) | ዞን | >> | 200 |
| | • ወረዳ ማስ/ጽ/ቤት (52 ፈፃሚ x 4ጊዜ x 1/2ቀን) | ወረዳ | >> | 104 |
| | • የመስክ ድጋፋዊ ክትትል ሪፖርት ማዘጋጀት | ክልል፣ ዞንና ወረዳ | >> | 16 |
| | • ግብረ መልስ መስጠት | >> | >> | **4** |
| **4.** | ሪፖርት ዝግጅት | | | |
| 4.1 | **የሪፖርት ማሰባሰቢያ ቅጽ ማዘጋጀትና ማሰራጨት** | ክልል ጽ/ቤት | ነሀሴ | 5 |
| 4.2 | **የሪፖርት ዝግጅት በቀበሌ ደረጃ** | | | |
| | • የሪፖርት ቅጽ ከወረዳ ለቀበሌ ማሰራጨት | ወረዳ | በየሩብ ዓመቱ | 4 |
| | • የቀበሌ ፈፃሚዎች ሪፖርት ያዘጋጃሉ (በአማካይ 3 ቀን) | ቀበሌ | >> | --- |
| | • በቀበሌ ደረጃ ሪፖርት ይመዘገባል | >> | >> | ---- |
| | • የቀበሌ ሪፖርት ይጠቃለላል | >> | >> | ---- |
| | • የተጠቃለለው የቀበሌ ሪፖርት ለወረዳ ይተላለፋል | >> | >> | ---- |
| 4.3 | **የሪፖርት ዝግጅት በወረዳ ደረጃ** | | | |
| | • የወረዳ ፈፃሚዎች ሪፖርት ያቀርባሉ (በአማካይ 3 ቀን) | ወረዳ | በየሩብ ዓመቱ | ---- |
| | • በወረዳ ደረጃ ሪፖርት ይመዘገባል | >> | >> | 16 |
| | • የቀበሌዎችና የወረዳ ፈጻሚዎች ሪፖርት ይጠቃለላል | >> | >> | 12 |
| | • የተጠቃለለ ሪፖርት ለም/ቤት ቀርቦ ይጸድቃል (በዓመት 2 ጊዜ) | >> | በየስድስት ወሩ | 2 |
| | • የተጠቃለለ የወረዳ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ይላካል | >> | በየሩብ ዓመቱ | 4 |
| 4.4 | **በዞን ደረጃ ሪፖርት ማጠቃለል** | | | |
| | • የዞን ፈፃሚዎች ሪፖርት ያቀርባሉ (በአማካይ 3 ቀን) | ዞን | በየሩብ ዓመቱ | ---- |
| | • በዞን ኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ ማስ/ጽ/ቤት ሪፖርት ይመዘገባል | >> | >> | 16 |
| | • የወረዳዎችና የዞን ፈፃሚ ሪፖርቶችን ማጠቃለል | >> | >> | 12 |
| | • የተጠቃለለ ሪፖርት ለም/ቤት ቀርቦ ይጸድቃል (በዓመት 2 ጊዜ) 30 | >> | በየስድስት ወሩ | 2 |
| | • የተጠቃለለ የዞን ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ይላካል | >> | በየሩብ ዓመቱ | 4 |
| 4.5 | **በክልል ደረጃ ሪፖርት ማጠቃለል** | | | |
| | • በክልል ደረጃ ያሉ ፈጻሚዎች ሪፖርት ያቀርባሉ | ክልል | በየሩብ ዓመቱ | |
| | • በክልል ደረጃ ሪፖርት ይመዘገባል | >> | >> | 20 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • ከየዞኖች የመጣውንና የክልል ፈጻሚዎችን ሪፖርት ማጠቃለል | >> | >> | 20 |
| | • የተጠቃለለ ሪፖርት ለክልል ኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤት ቀርቦ ይፀድቃል | >> | በየስድስት ወሩ | 2 |
| | • የተጠቃለለ የክልል ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ይላካል | >> | በየሩብ ዓመቱ | 4 |
| **5** | **የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ** | | | |
| **5.1** | • ለዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት | በክልል | ጥርና ሀምሌ | **4** |
| | • ለተሳታፊዎች ጥሪ እንዲተላለፍ ማድረግ | >> | >> | **1/2** |
| | • ለግምገማው የሚቀርበውን ሪፖርት ማደራጀት | >> | >> | **6** |
| | • ለተሳታፊ የሚሰራጭ ሪፖርት ማዘጋጀት | >> | >> | **1/2** |
| | • የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማውን ማካሄድ | >> | >> | **18** |
| **5.2** | • ለዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት | ዞን | ጥርና ሀምሌ | **4** |
| | • ለተሳታፊዎች ጥሪ እንዲተላለፍ ማድረግ | >> | >> | **1/2** |
| | • ለግምገማው የሚቀርበውን ሪፖርት ማደራጀት | >> | >> | **6** |
| | • ለተሳታፊ የሚሰራጭ ሪፖርት ማዘጋጀት | >> | >> | **1/2** |
| | • የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማውን ማካሄድ | >> | >> | **4** |
| **5.3** | • ለዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት | በወረዳ | ጥርና ሀምሌ | **4** |
| | • ለተሳታፊዎች ጥሪ እንዲተላለፍ ማድረግ | >> | >> | **1/2** |
| | • ለግምገማው የሚቀርበውን ሪፖርት ማደራጀት | >> | >> | **6** |
| | • ለተሳታፊ የሚሰራጭ ሪፖርት ማዘጋጀት | >> | >> | **1/2** |
| | • የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማውን ማካሄድ | >> | >> | **2** |
| **6** | **ጥሩ ተሞክሮዎችን ማስፋትና የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና ማካሄድ** | | | |
| | **ጥሩ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት** | | | |
| | • ጥሩ ተሞክሮ ለማስፋት ቢጋር ማዘጋጀት | ክልል | ሀምሌ | **3** |
| | • ጥሩ ተሞክሮዎችን መለዮት | >> | ሀምሌና ነሀሴ | **30** |
| | • ጥሩ ተሞክሮዎችን ለማስፋት በሚያስችል መልኩ ማዘጋጀት | >> | >> | **20** |
| | • ጥሩ ተሞክሮዎችን ማሰራጨትና ማስፋት | >> | መስከረም | **2** |
| | **የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና ማካሄድ** | | | |
| | • ውጤታማነታቸው የሚመዘኑ ፕሮግራሞችን መለዮት | ክልል | ሀምሌ | **3** |
| | • የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና እንዲካሄድ የምዘ ቢጋር ማዘጋጀት | >> | >> | 3 |
| | • አሸናፊውን መለዮት | >> | >> | **2** |
| | • ምዘናው ሲካሄድ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | >> | ከነሀሴ - ህዳር | **10** |
| | • የምዘናውን ውጤት ለሚመለከታቸው ማሰራጨትና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ | >> | ታህሳስ | **10** |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1.4 | ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች የሚሰባሰበው ሀብት ወደ ባንክ እንዲገባ ክትል ማድረግና የገባ መሆኑን ማረጋገጥ | 4.00 | | |
| 1.5 | **የሃብት ድልድል ማድረግ** | | | |
| | የበጀት ድልድል ለማድረግ ለዞን ማስ/ጽ/ቤቶችና ለክልል ፈጻሚ አካላት ጥሪ ይተላለፋል፣ | 0.50 | | |
| | ለውይይት መነሻ የሚሆን የሀብት ድልድል ፕሮፖዛል ይዘጋጃል | 8.00 | | |
| | በቀረበው መነሻ ሀሳብ መሰረት በተሳታፊዎች ውይይት ተካሂዶ ድልድሉ ይሰራል | 2.50 | | |
| | የተሰራውን የሀብት ድልድል ለሚመለከታቸው ማሳወቅ | 0.50 | | |
| | በዕቅድ ዝግጅት ወቅት ያልታዩ የአፕሬዛል ስራዎች | 80.00 | | |
| 2 | **የመስክ ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ** | | | |
| | የክትትል ቢጋር ማዘጋጀት | **2.00** | | |
| | የመስክ ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ(ክልል ማስ/ጽ/ቤት (120 ፈፃሚ x 4ጊዜ x 1ቀን)) | **720.00** | | |
| | የመስክ ድጋፋዊ ክትትል ሪፖርት ማዘጋጀት | **16.00** | | |
| | ግብረ መልስ መስጠት | **4.00** | | |
| **3** | ***ሪፖርት ዝግጅት*** | | | |
| 3.1. | የሪፖርት ማሰባሰቢያ ቅጽ ማዘጋጀትና ማሰራጨት | 5.00 | | |
| 3.2 | ***ሪፖርት ማጠቃለል*** | | | |
| | በክልል ደረጃ ያሉ ፈጻሚዎች ሪፖርት ያቀርባሉ | ----- | | |
| | በክልል ደረጃ ሪፖርት ይመዘገባል | 20.00 | | |
| | ከየዞኖችና ከክልል ፈጻሚዎች የመጣውን ሪፖርት ማጠቃለል | 20.00 | | |
| | የተጠቃለለው ሪፖርት ለክልል ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤት ቀርቦ ይፀድቃል | 2.00 | | |
| | ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት መላክ | 4.00 | | |
| **4** | **የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ** | | | |
| | ለዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት | **4.00** | | |
| | ለተሳታፊዎች ጥሪ እንዲተላለፍ ማድረግ | **0.50** | | |
| | ለግምገማው የሚቀርበውን ሪፖርት ማደራጀት | **6.00** | | |
| | ለተሳታፊ የሚሰራጨውን ሪፖርት ማዘጋጀት | **0.50** | | |
| | የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማውን ማካሄድ | **18.00** | | |
| | **ጥሩ ተሞክሮዎችን ማስፋትና የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና ማካሄድ** | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **ጥሩ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት** | | |
| | • ጥሩ ተሞክሮ ለማስፋት የምዘና ቢጋር ማዘጋጀት | **3.00** | |
| | • ጥሩ ተሞክሮዎችን፣ በአፈፃፀም የታዩና ሌሎች ሊመዘኑ የሚገባቸውን መለየት | **30.00** | |
| | • ጥሩ ተሞክሮዎችን ለማስፋት በሚያስችል መልኩ ማዘጋጀት | **20.00** | |
| | • ጥሩ ተሞክሮዎችን ማሰራጨትና ማስፋት | **2.00** | |
| | **የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና ማካሄድ** | | |
| | • ውጤታማነታቸው የሚመዘኑ ፕሮግራሞችን መለየት | **3.00** | |
| | • የፕሮግራም ውጤታማነት ምዘና እንዲካሄድ የምዘና ቢጋር ማዘጋጀት | **2.00** | |
| | • አሸናፊውን መለየት | **2.00** | |
| | • ምዘናው ሲካሄድ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | **10.00** | |
| | • የምዘናውን ውጤት ለሚመለከታቸው ማሰራጨትና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ | **10.00** | |
| | **በዕቅድ ለተያዙ ተግባራት በክልል ደረጃ በዓመት የሚወሰደው ጊዜ** | **1092.00** | |
| | | | |
| | **በክልል ደረጃ በዓመት የሚወሰደው ቀን** | **1201.00** | |

ለ) **በዞን ማስ/ጽ/ቤት ደረጃ**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • ለተሳታፊ የሚሰራጭ ሪፖርት ማዘጋጀት | **0.50** | | |
| | • የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማውን ማካሄድ | **4.00** | | |
| | **ለእያንዳንዱ ዞን በአመት የሚወስደው ጊዜ** | **325.00** | | |
| | | | | |
| | **በዞን ደረጃ በዓመት የሚወስደው ጊዜ** | **358.00** | | |

ሐ) **<u>በወረዳ ማስ/ጽ/ቤት ደረጃ</u>**

| ተ.ቁ | የሂደቱ ዋና ዋና ተግባራትና ዝርዝር ስራዎች | ስራዎቹ የሚወስዱት ቀናት | ተግባርና ኃላፊነት ማመላከት | ተፈላጊ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **ዕቅድ ማጠቃለል** | | በተ.ቁ. 1፣ 2፣ 3፣ 4 እና 5 የተመለከቱትን ተግባራት ማከናወን | • በኢኮና በሶሲአ በስታቲ በሕብረ በማኔጀ የትምህ የመጀመ ከዚያ እንዲሁ ለመጀመ ዓመትና ያለው ወይም 2 ዓመ ዲፕሎማ አግባብ ልምድ የኤችአ ማቀድና የእንግለ ክህሎት |
| **1.1** | **የዕቅድ አዘገጃጀት ገለፃ ( ወረዳ ለየቀበሌ ተጠሪዎች)** | | | |
| | • የዕቅድ ማዕቀፉንና ማብራሪያዎቹን በተሳታፊዎች ቁጥር ማባዛትና ቅድመ ዝግጅት | 1.00 | | |
| | • ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍና ማድረስ | 3.00 | | |
| | • ገለፃ መስጠት፣ የዕቅድ ማዕቀፉን ማሰራጨት | 1.00 | | |
| **1.2** | **ዕቅድ ዝግጅት በወረዳ ደረጃ** | | | |
| | • የቀበሌዎችን ዕቅድ ማጠናቀር | 2.00 | | |
| | • ለወረዳ ፈፃሚዎች ጥሪ ይተላፋል | 0.50 | | |
| | • ለወረዳ ፈጻሚዎች በተጠቃለለው የቀበሌ ዕቅድ ላይ ገለፃ ይካሄዳል | 0.50 | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የመስክ ድጋፋዊ ክትትል ሪፖርት ማዘጋጀት | 16.00 | | |
| | ግብረ መልስ መስጠት | 4.00 | | |
| **3** | **ሪፖርት ዝግጅትና ማጠቃለል** | | | |
| | • ከወረዳ ወደ ቀበሌ የሪፖርት ቅፅ ማሰራጨት | 4.00 | | |
| | • የወረዳ ፈፃሚዎች ሪፖርት ያቀርባሉ (በአማካይ 3 ቀን) | ---- | | |
| | • በወረዳ ኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ ማስ/ጽ/ቤት ሪፖርት ይመዘገባል | 16.00 | | |
| | • የቀበሌዎችና የወረዳ ፈፃሚ ሪፖርቶችን ማጠቃለል | 12.00 | | |
| | • የተጠቃለለ ሪፖርት ለም/ቤት ቀርቦ ይጸድቃል (በዓመት 2 ጊዜ) | 2.00 | | |
| | • የተጠቃለለ የወረዳ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ይላካል | 4.00 | | |
| **4** | **የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ** | | | |
| | • ለዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት | **4.00** | | |
| | • ለተሳታፊዎች ጥሪ እንዲተላለፍ ማድረግ | **0.50** | | |
| | • ለግምገማው የሚቀርበውን ሪፖርት ማደራጀት | **6.00** | | |
| | • ለተሳታፊ የሚሰራጭ ሪፖርት ማዘጋጀት | **0.50** | | |
| | • የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማውን ማካሄድ | **2.00** | | |
| | **ለእያንዳንዱ ወረዳ በአመት የሚወስደው ጊዜ** | **239.25** | | |
| | | | | |
| | **በወረዳ ደረጃ በዓመት የሚወስደው ጊዜ** | **240.00** | | |

## መ) በቀበሌ ደረጃ

በቀበሌ ደረጃ ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ያሉት አንድ ግብረ-ሃይል ይኖራል፡፡ አባላቱም በዋነኝነት የትምህርት፣ ግብርና ሴቶችና ወጣቶች ዘርፍን ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡ የግበረ ኃይሉ ተጠሪነትም ለቀበሌው

ዋና አስተዳዳሪው ሲሆን የግብረ-ሃይሉ ሰብሳቢ የቀበሌው ስራ አስኪያጅ ሆኖ የግበረ-ሃይሉ ፀሐፊ የቀበሌው የጤና ኤክስቴንሽን ኃላፊዋ ትሆናለች፡፡ በዚህ አደረጃጀት ሁሉም የኤችአይቪ መከ/መቆ/ ስራዎች በቀበሌ ደረጃ አማካኝነት ይከናወናሉ፡፡

## • <u>የሰው ኃይል ለመወሰን የተወሰደ ታሳቢ</u>

ስሌቱ የተሠራው በዓመት ውስጥ በአማካይ 1700 የሥራ ሰዓታት ቢኖርሩ እና አንድ ሰው በቀን 8 ሰዓት ይሠራል ከሚል መነሻ ነው። ይኸውም፡-

- የዓመቱ ጠቅላላ ቀናት = 365
- ከዚህ ውስጥ ሥራ የማይሰራባቸው ቀናት = 146 ቀናት ከ52 ሰዓት(ቅዳሜና እሁድ=104 ቀናት፣ የሕዝብ በዓላት=12 ቀናት፣ የዓመት እረፍት=30 ቀናት፣ በየሳምንቱ ዓርብ ሥራ የማይሰራባቸው=52 ሰዓታት)
- ስለዚህ በዓመት የሥራ ቀናት= 365-146 ቀን ከ52 ሰዓት= 219 ቀን X8 - 52 = 1700 ሰዓታት ይሆናሉ ማለት ነው።
- በዚህ ስሌት መሠረት የሥራ ሂደቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለማከናወን የሚያስፈልገው የሰው ኃይል
    - በክልል 5
    - በዞን እንደ ዞኑ ስፋት(1ወይም 2)
    - በወረዳ 1

## • <u>በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ የስራ ሂደት ነባሩ ድርጅታዊ መዋቅር</u>

የወረዳ
ማስተባበርያ ጽ/ቤቶች
የዞን ማስተባበርያ ጽ/ቤቶች
ሜይንስትሪሚንግና ፓርትነርሺፕ
ድጋፍና ክብካቤ
ፕሮግራሞች ማስተባበርያ ክፍል
የክትትልና ግምገማ ክፍል

ፋይናንስ ክፍል

የሕዝብ ንቅናቄ
ዕቅድና ፕሮጀክት ምዘና

የቀበሌ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ

- <u>በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ የስራ ሂደት አዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር</u>

የስራ ሂደቱ መሪ
(የክልል ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ)
(Process Leader)

የስራ ሂደቱ ባለቤት
(Process Owner)

የስራ ሂደቱ ፈፃሚዎች
(Generalists)

የዞን የስራ ሂደቱ ፈጻሚዎች

(Generalists)

የወረዳ የስራ ሂደቱ ፈጻሚ
(Generalists)

የቀበሌ ግብረ-ኃይል አስተባባሪ

- **<u>አዲሱ የስራ ሂደት አዲስ መሆን ያለመሆኑን ማረጋገጥ</u>**

**የማረጋገጫ መስፈርቶች**

| ተ.ቁ. | መስፈርት | በነባሩ | በአዲሱ |
|---|---|---|---|
| 1 | **መሰረታዊ ለውጥ ለመሆኑ የተሰበሩ ህጎች** | | |
| | ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ<br>አዋጅ ቁ. 73/94 አንቀጽ15ን/ቁ.9 | ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ዕቅድ ያዘጋጃል ይተገብራል | ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ማስተባበሪያ ያስተባብራል ሲፈጽሙም ይከታተላል ሪፖ |
| | አዋጅ ቁ. 73/94 አንቀጽ 25-26. | ዕቅድና ሪፖርት በም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤና ስራ አመራር ይጸድቃል | በቀበሌው ግብረሀይል በሚመራ አደረጃጀት አስተዳደር ይጸድቃል |
| | አዋጅ ማሻሻያ | እያንዳንዱ ሴክተር የኤችአይቪ ኤድስን መከ/መቆ/ስራ እንዲያቅድና ሪፖርት እንዲያደርግ ተጠያቂ አልነበረም | ሁሉም ሴክተር የኤችአይቪ ኤድስን መከ/ እንዲያደርግ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ይሆ |
| | አዋጅ ቁጥር 73/94 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀፅ 12 እና 13 | ከፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በየደረጃው በሚገኙ የስራ አመራር ወይም የሪቪው ቦርድ ኮሚቴዎች መታየት እንዳለበት በአዋጁ ተመላክቷል | በየደረጃው የሚገኙ የማስ/ጽ/ቤት ባለሙ ምዘናው በእነሱ አማካኝነት የሚካሄድ በሚልበት ጊዜ ደግሞ በሪቪው ቦርድ ለ ላይ ተሻሽሎ ቢቀመጥ |

5. አዲስ ሃሳብ ማመንጨት ........ 11
5.1 አዳዲስ የፈለቁ ዝርዝር ሀሳቦች ........ 11
5.2 በተደራጀ መልክ የወጡ አዲስ ሀሳቦች ........ 16
6. በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የስራ ሂደት ........ 18
6.1. አማራጭ 1 የስራ ፍሰት (High Level Map) ........ 18
6.2 አማራጭ 2 የስራ ፍሰት (High Level Map) ........ 19
6.3 አማራጭ 3 የስራ ፍሰት (High Level Map) ........ 20
7. አዳዲስ አማራጭ ሀሳቦችን የማወዳደሪያ መስፈርቶችና የተገኘ ውጤት ........ 21
8. የአማራጭ የስራ ሂደቶች የብቃት ማረጋገጫ ዳሰሳ ........ 22
9. የአዲሱ የስራ ሂደት ዝርዝር የስራ ፍሰት (Detail Map) ........ 24
10. አዲሱ የስራ ሂደት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ........ 26
11. አዲሱ የስራ ሂደት ከነባሩ የሚለይባቸው ነጥቦች ........ 27
12. በአዲሱ የስራ ሂደት ጥናት መሰረት የሚቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የሚገባቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመርያዎች 29
13. በአዲሱ የስራ ሂደት የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት ........ 30
14. በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የስራ ሂደት የአፈፃፀም ስታንዳርድና ፈፃሚዎች ........ 34
15. በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የስራ ሂደት የአፈፃፀም ስታንዳርድና ፈፃሚዎች በደረጃና በችሎታ የተለየ 39
16. የሰው ኃይል ለመወሰን የተወሰደ ታሳቢ ........ 45
17.በጋራ የማሳቀድ፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የስራ ሂደት ነባሩ ድርጅታዊ መዋቅር ........ 45
18. በጋራ የማሳቀድና ክትትል የስራ ሂደት አዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር ........ 45
19. አዲሱ የስራ ሂደት አዲስ መሆን ያለመሆኑን ማረጋገጥ ........ 45